በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት

የ6ኛ ክፍል ግብረገብ ሞዴል ፈተና

ሚያዝያ, 2016ዓ.ም/ አፕሪል 2024 እ.ኤ.አ

የጥያቄ ብዛት: 40 **የተፈቀደው ሰዓት: - 1 ሰዓት**

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ **የግብረገብ** ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 **ሰአት** ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ስለግብረገብ ምሉዕነት ትክክል አይደለም

   ሀ. የግብረገብ ምሉዕነት በየዕለቱ ተገቢነት ያላቸው ድርጊቶችን መፈፀም ነው።

   ለ. መሰረታዊ የሚባሉት ባህርያትን ተለዋዋጭ በሆነ መንገድ ማሳየት ነው።

   ሐ. ሀቀኝነት ታማኝነት በወጥነት ማሳየትን የሚያመለክት ነው።

   መ መሰረታዊ ግላዊ እምነቶችን ኢ-ተለዋዋጭ በሆነ መንገድ መፈፀም ነው።

2. ግብረገባዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሌሎች ሰዎች አስተያየትና ይሁንታን አለመጠበቅ ምንን ይገልፃል ?

   ሀ. ለሌሎች ማሰብ ሐ. ድፍረትን

   ለ. ፍርሀት መ. ኢ-ተለዋዋጭነት

3. በግላችን ለምንወስናቸው ውሳኔዎች ውጤቱ ጥሩም ሆነ መጥፎ ድርሻን መውሰድ

   ሀ. አ-ተለዋዋጭ ሐ. ወጥነት

   ለ. ሀቀኝነት መ. ኃላፊነትን መውሰድ

4. ቀሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምሉዕነት ጥቅም ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው ?

   ሀ. አንዱ ለሌላው ለውጥ እንቅፋት መሆን

   ለ. ውሳኔዎችን የመወሰን ክህሎትን ማሳደግ

   ሐ. ጠንካራ ሰራተኞችን ማፍራት

   መ. ችግሮችን የመፍታት ብቃት ማዳበር

5. የግብረገብ ምሉዕነት ጠቀሜታን የሚገልፀው የቱ ነው?

   ሀ. ማህበራዊ ትስስርን ማጠናከር ሐ. የገቡልንን ቃል መፈጸም

   ለ. ፈታኝ ሁኔታዎችን መጋፈጥ መቻል መ. ሁሉም መልስ ናቸው

6. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የግብረገብ ምሉዕነት ያለው ሰው ባህሪ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የማይችሉትን ነገር ለማድረግ ቃል ይገባሉ

   ለ. ቃላቸውን የማይጠብቁ ናቸው

   ሐ. ህይወታቸውን በመርሆች የሚመሩ ናቸው

   መ. ችግሮችን ይሸሻሉ

7. ቀጥሎ ከቀረቡት መካከል የግብረገብ ምሉዕነት ባለመኖሩ ምክንያት የሚከሰተው የቱ ነው?

   ሀ. የባህሪ እና የተግባር አለመገናኘት ሐ. የሌሎችን ጥቅም ማግኘት

   ለ. ለሰዎች አክብሮት መስጠት መ. ውስጣዊ ደስታ ማግኘት

8. አንድ ህግ ቋሚ መሆን አለበት ስንል ምን ማለታችን ነው ?

   ሀ. መቀየር ፣መሻሻል አይችሉም

   ለ. ለረዥም ጊዜ አያገለግልም

   ሐ. ለሁሉም ማህበረሰብ እኩል አያገለግሉም

   መ. አንድ ቦታ ብቻ መቀመጥ አለባቸው

9. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለህግ ተገዢ የመሆን ጠቀሜታን አያመለክትም ?

   ሀ. የሰላም መጠበቅ ሐ. በፍትሐዊነት አለመስተናገድ

   ለ. የሉአላዊነት መከበር መ . የዜጐች መብት መረጋገጥ

10.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ስለ ህግ አስፈላጊነት ትክክል ነው ?
ሀ. ህግ የዜጎች ይሁንታ መገለጫ ነው
ለ. ሉአላዊነት የነፃነት ምልክት ነው
ሐ. ህግ ወንጀል ፈጻሚዎች ላይ ክልከላ ያደርጋል
መ. ህግ ነጻነት ገዳቢ በመሆኑ መከበር የለበትም
11.ለህግ ተገዢ የሆነ ሰዉ ባህርያትን የማይገልጸው የቱ ነው ?
ሀ. ህግ የግል ጥቅምን ብቻ እንደሚያስጠብቅ ይረዳሉ
ለ. የመብቶቻቸውንና የኃላፊነታቸውን ገደብ ያውቃሉ
ሐ. የህግ መጠበቅ የህዝቦችን ይሁንታ መጠበቅ ነው
መ. የህጎች መጠበቅ የተሻለ ህይወት እንደሚያመጣ ያምናሉ
12.የአንድ ሀገር ዜጎች ለህግ ተገዢ መሆናቸውን የሚገልፀው የትኛው ነው?
ሀ. ደንቦችን ማክበር እንዳለባቸው ያውቃሉ
ለ. ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል
ሐ. የሀገሪቱን ህግ ለማስከበር ቁርጠኛ ናቸዉ
መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ
13.ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ለባለስልጣናት ገንዘብ መስጠት
ሀ. ዝምድና ለ. ማጭበርበር ሐ. ጉቦ መ. ወገንተኝነት
14.ቀጥሎ ከቀረቡት መካከል ግብር ስወራን የማያካትተው የቱ ነው?
ሀ. ሀሰተኛ የግብር ሰነድ ሐ. መረጃን በአግባቡ ማደራጀት
ለ. ገቢን አሳንሶ መቅረብ መ. የተጋነነ ወጪ
15.ከሚከተሉት መካከል የመልካም ባህሪ ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነዉ?
ሀ. ጠንካራ ሠራተኛነ አለማድነቅ ሐ. ላላቸው ነገር አመስጋኝ መሆነ
ለ. ፈቃድን መጠየቅ መ. ትሁት መሆን
16.አጭበርባሪነትን እና ሌብነትን ማስወገድ መቻል ከሚከተሉት የትኛውን ይገልፃል ?
ሀ. ምሉዕነት ለ. ሀቀኝነት ሐ. ታማኝነት መ. ተጠያቂነት
17.ራስን መንከባከብ እና ስለራስ መልካም ስሜት መያዝ_____ይባላል።
ሀ . ለአስተሳሰባችን ክቡር መስጠት ሐ. ለአካላዊ ሰውነታችን ክብር መስጠት
ለ. ለጤናችን ክብር መስጠት መ. ለራስ ክብር መስጠት
18.ከሚከተሉት ውስጥ የመልካም ባህሪ መላበስን አስፈላጊነት የሚገልፀው የቱ ነው ?
ሀ. በሰዎች ዘንድ አሉታዊ ምስል መፍጠር ሐ. ስለራስ ትክክለኛ እሳቤ አለመያዝ
ለ. የመበለጥ ስሜትን ማጎልበት መ. የእርካታ መንፈስን ማሳደግ
19.በህዝቦች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር የሚያደረገው ህግ በማን ይዘጋጃል ?
ሀ. በህግ አውጪ ሐ. በጠቅላይ ሚኒስትር
ለ. በህግ አስፈፃሚ መ. በህግ ተርጓሚ
20.ፍላጎቶችን ፣ ልምዶችን እና ሀሳብን የመግታት ብቃት ---------- ይባላል ።
ሀ. ኃላፊነትን መውሰድ ሐ. ተለዋዋጭነት
ለ. ራስን መቆጣጠር መ. ተጠያቂነት
21.የማህበረሰቡ ችግሮች ላይ ትኩረት አድርጎ መፍትሔ ለማምጣትና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እንቅስቃሴ_____ነው ።
ሀ. ኢኮኖሚያዊ ተግባር ሐ. መንግስታዊ ተግባር
ለ. ማህበራዊ ተግባር መ. ፖለቲካዊ ተግባር

22.ለሌሎች ጥቅም የራስን ጊዜና ጉልበተን በሙሉ ፈቃደኝነትና ቁርጠኝነት ማዋል ነው?
ሀ. በንግድ ስራ መሰማራት ሐ. የውትድርና አገልግሎት
ለ. የማስተማር ስራ መ. በጎ አድራጎት
23.ከሚከተሉት ውስጥ የበጎ አድራጎት ሥራ አስፈላጊነት አይደለም ?
ሀ. የግል ትርፍን ማግኘት ሐ. የመረዳዳት መንፈስን ይፈጥራል
ለ. የተቸገሩትን ለመርዳት መ. የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል
24.ቀጥሎ ከቀረበት አማራጮች ውስጥ ትርፍ ጊዜን ለጋራ ጥቅም የምናውልበት ተግባር የትኛው ነው?
ሀ. በአካባቢ ዕዳት መሳተፍ ሐ. መሰረተ ልማቶችን በመደገፍ
ለ. አቅመ ደካሞችን በማገዝ መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ
25.በሰዎችና በሀገሮች መካከል መሻሻጥና ምርት የመለዋወጥ መንገድ _____ነው ።
ሀ. ነጋዴ ለ. ገበያ ሐ. ንግድ መ. መደብር
26.ከሚከተሉት ውስጥ መሠረታዊ የግብር የገቢ ምንጭ ያልሆነው የቱ ነው ?
ሀ. የፋይናንስ ገቢ ሐ. ከግለሰቦች የ ንግድ ትርፍ
ለ. ከሽልማት መ. ከቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት
27.ከተዘረዘሩት መካከል የታማኝ ግብር ከፋዮች ባህሪ የማይሆነው የቱ ነው ?
ሀ. ግብር የመንግስት ዋና የግብር ምንጭ መሆኑን ይገነዘባሉ
ለ. ለግብር ሰብሳቢዎች የገቢ መጠናቸውን ይደብቃሉ
ሐ. መሰረተ ልማቶች የግብር ውጤት መሆናቸው ይረዳሉ
መ. ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታ መሆኑን ያውቃሉ
28.ዘመናዊ የቁጠባ ተቋም የሆነው የቱ ነው ?
ሀ. እድር ለ. እቁብ ሐ. ባንክ መ. መዋጮ
29.ከሚከተሉት ውስጥ የቁጠባ ጠቀሜታ ሊሆን የማይችለው የቱ ነው?
ሀ. ለት/ቤት ክፍያ ይውላል ሐ. ለድንገተኛ ወጪ
ለ. ኑሮን ለማሻሻል መ. ብድር ለመጠየቅ
30.በሀገራችን በዋናነት የሚጠቀስ ባህላዊ የመቆጠቢያ መንገድ የቱ ነው ?
ሀ. እድር ለ. እቁብ ሐ. የመድህን ድርጅት መ. የፋይናንስ ተቋም
31.የሀገር ፍቅር ምንነትን የበለጠ የሚገልፀው ሀሳብ የቱ ነው?
ሀ. ተፈጥሮአዊ ሀብቶችን ማድነቅ ሐ. ለሀገር እድገት ጠንክሮ መስራት
ለ. የሀገር ታሪክ በጽሑፍ ማቅረብ መ. ጠላትን በጦርነት መዋጋት
32.ዜጎች ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር የሚገልፁበት ሁኔታ የቱ ነው?
ሀ. ሙስናን በመዋጋት ሐ. በሀገር መኩራት
ለ. ጀግኖችን ማክበር መ. ሁሉም
33.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የሀገር ወዳድነት ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው ?
ሀ. የግል ፍላጎትን ማስቀደም ሐ. አንድነትን ለማስጠበቅ
ለ. የሀገር እድገትን ለማፍጠን መ. ለዘላቂ ሰላም
34.ልጆች የሀገር ፍቅር እንዲኖራቸው የቤተሰብ ሚና የሆነው የቱ ነው?
ሀ. የሀገራቸውን ታሪክና ባህል ማሳወቅ
ለ. ስለ ብሔራቸው ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ
ሐ. ለህዝብ ክብር እንዳይሰጡ መምከር
መ. የግል ፍላጎታቸው ላይ እንዲያተኩሩ መምከር

35.በአሜሪካ ለሚኖሩ የ ጥቁር ህዝቦች ሰብዓዊ መብት መከበር የታገለ መሪ ነበር ?

ሀ. ኔልሰን ማንዴላ ሐ. መሀተበ ጋንዲ

ለ. ማዘር ትሬዛ መ. ማርቲ ሉተር ኪንግ

36.ቀጥሎ ከቀረበት ውስጥ የአንድ ሀገርን ህልውና ለማስጠበቅ እጅግ ጠቃሚ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ጀግንነት ለ. የእርስ በርስ ጦርነት ሐ. ቆራጥነት መ. መስዋትነት

37.አንድ ሰው ከጭንቀትና ከፍርሀት ነፃ መሆኑን የሚገልጸው የሰላም ደረጃ የትኛው ነው ?

ሀ. ሀገር አቀፍ ሰላም ሐ. የግለሰብ ሰላም

ለ. አለም አቀፍ ሰላም መ. የማህበረሰብ ሰላም

38.ነገሮችን ከሌሎች ሰዎች ጋር የመጠቀም ችሎታ ምን ይባላል ?

ሀ. ስምምነት ለ. ማጋራት ሐ. ውይይት መ. ትዕግስት

39. አለመመግባባቶችን ለመፍታት የሚጠቅመው የሰላም ባህሪ የማይሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ይቅርባይነት ለ. ግጭት ሐ. ተንኮል መ. ጥላቻ

40.ከሚከተሉት ውስጥ የመተባበር እሴት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ግልፅነት ለ. አብሮነት ሐ. ሌሎችን መንከባከብ መ. ሁሉም

መልካም ፈተና